# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አምተኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺ፲፩

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 65
ADDIS ABABA May 8 th, 2019


<u>ማውጫ</u>


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፱/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረገውን የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት ማፀደቂያ አዋጅ…………………....ገጽ፲፩ሺ፪፻፶፬


**<u>CONTENT</u>**


Proclamation No.1129/2019

Kigali Amendment Agreement to the Montreal Protocol Ratification Proclamation...........................................Page 11254


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፱/፪ሺ፲፩

## <u>በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረገውን የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኦዞን ንጣፍን ከመሳሳት ለመከላከል የወጡትን የቬና ኮንቬንሽንና የሞንትሪያል ፕሮቶኮል በማፀደቅ የስምምነቶቹ አባል አገር በመሆኗ፤

ሞንትሪያል ፕሮቶኮል የኪጋሊ ማሻሻያ ጥቅምት ፭ /፪ሺ፱ ዓ.ም በሞንትሪያል ፕሮቶኮል አባል አገራት ጉባኤ በኪጋሊ ከተማ የፀደቀ በመሆኑ፤

ይህንኑ አዋጅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡

## PROCLAMATION NO.1129/2019

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE KIGALI AMENDMENT AGREEMENT TO THE MONTREAL PROTOCOL</u>

**WHERE AS** ,The Federal Democratic Republic of Ethiopia is party to the Vienna Convention and Montreal Protocol for the preservation of the Ozone Layer,

**WHEREAS,** the Kigali Amendment to the Montreal Protocol is adopted by the Conference of the State Parties to the Montreal Protocol on 15th day of October 2016 in Kigali;

**WHERE AS** ,the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Proclamation at its session held on the 2nd day of April 2019;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የሞንትሪያል ፕሮቶኮል የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት ማፀደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፳፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረገው የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሞንትሪያል ፕሮቶኮል የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነትን የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Kigali Amendment Agreement to the Montreal Protocol Ratification Proclamation No. 1129/2019."

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Kigali Amendment Agreement to the Montreal Protocol is hereby Ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Environment, Forest and Climate Change Commission of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Kigali Amendment Agreement to the Montreal Protocol.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon its Publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On the 8th Day of May , 2019**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**